በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

የካቲት 9 ቀን 2011
አዲስ አበባ
መግለጫ

# 63ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 63ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በገንዘብ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ የብድር ስምምነቶችና ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገ የብድር ስምምነት፤ ለሴቶች ንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል የተደረገ የብድር ስምምነት፣ ለአነስተኛና መካከለኛ ከተሞች ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮግራም ከፊል ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የብድር ስምምነት እና ለዘላቂና አካታች የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለት ዕድገት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረጉ የብድር ስምምነቶች ለም/ቤቱ ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑንና ለአገራችን የሚያስገኙትን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ የቀረቡትን የብድር ስምምነቶችና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆቹን ተቀብሎ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡
2. ም/ቤቱ ቀጥሎ የተወያየው የኢሚግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ እና የብሄራዊ መታወቂ አገልግሎት አሰጣጥ ከስራ ባህሪ አንጻር በአንድ ኤጀንሲ እንዲደራጁ በመደረጉ

የኢሜግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃትን ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ ደንብ በሰላም ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቀርቧል። ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል::

//